# የሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት

# ፕሮግራም

መስከረም፤ 2005
October, 2012

ዋሽንግቶን ዲሲ - **Washington DC**

# <u>ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ፕሮግራም፣</u>

## <u>መግቢያ፣</u>

ኢትዮጵያ ረጅም የአገርነትና ተከታታይነት ያለው የመንግሥት ታሪክ ካላቸው ጥቂት አገሮች አንዷ ናት፡፡ የረጅም ዘመን አገርነቷና የተከታታይ በሀወርታዊ መንግሥት ባለቤት መሆኗ፣ በጥንታዊ ሥልጣኔ የቴክኖሎጂ ቅሬቶቿና በራሷ የጽሁፍ ቋንቋ የተገለጸ ነው፡፡ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙት የአክሱም ሀውልት፣ የላሊበላ ውቅር አብያተክርስቲያናት፣ የጎንደር ቤተመንግሥቶችና ልዩ ልዩ ጥንታዊ መገልገያ መሣሪያዎች፣ የረጅም ዘመን ታሪኳ ቋሚ ነቃሾች ናቸው፡፡ በቅርቡ በምሥራቅ ኢትዮጵያ የተገኘው ጥንታዊው የሐርላ ሥልጣኔ መገለጫ የሆኑ የገንዘብ ምስሎች፣ በጉርሱም የተገኙት የጎዳ ሮሪስ፣ ከሐረር ከተማ በስተምሥራቅ የተገኘው የሣካ ሻዐሪፍ ሥዕሎች፣ እንዲሁም በአርኬዎሎጂ ጥናትና ምርምር ከምድር ውስጥ ተቆፍረው የተገኙት የድንጋይ ላይ ጽሑፎች የኢትዮጵያን ረጅም ዘመን የታሪክ ባለቤትነት የሚያረጋግጡ ሕያው ማስረጃዎች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ረጅም ሀገራዊነትና የመንግሥትነት ታሪክ ልዩ የሚያደርገው ጥንታዊ ሥልጣኔና ተከታታይነቱን በጠበቀ መንግሥትነት መኖር ብቻ ሳይሆን፣ አገሪቱ የብዙ ነገዶች አገር መሆኗና ነገዶቿ በኢትዮጵያዊነት መዕቀፍ ውስጥ ደስታና መከራን፣ ሰላምና ጦርነትን፣ስደትና ሰፈራን፣ የተጋሩ የጀግኖችና የኩሩ ሕዝብ አገር በመሆኗ ጭምር ነው፡፡

የአገሪቱና የመንግሥቱ ተከታታይነት፣ የሕዝቡ በሀወርታዊነት እንዲሁ በልዩ ተዓምር ዕውን የሆነ አይደለም፡፡ ተስፋፊነትንና ቅኝ ገዥነትን መነሻና መድረሻ አድርገው በተደጋጋሚ ጊዜያት ሊወሩን፣ ቅኝ ተገዥ ሊያደርጉን፣ ነፃነታችንን ሊገፉን፣ ሃይማኖታችን ሊያስለውጡን፣ ሊነጣጥሉንና ተዋራጅ ሊያደርጉን፣ወራሪና ቅኝ ገዥ ሠራዊት አሠልጥነውና አደራጅተው ባሕር አቋርጠው፣ ድንበር አልፈው የመጡ የፖርቱጋልን፣ የግብፅንና የጣሊያንን ወራሪዎችና ቅኝ ገዥዎችን ፍላጎት ያከሸፈው ሕዝቡ በየዘመኑ ከነበሩ ንጉሦችና የአካባቢው ገዥዎች ሥር በመሰለፍ በከፈለው ውድና ትክ-የለሽ የሕይወት፣ የአጥንትና የደም ዋጋ ነው፡፡ ይህ የሕይወት ዋጋ የተከፈለበት መስዋዕትነት የኢትዮጵያ አንድነትና በሀወርታዊነት ለረጅም ተከታታይ ዘመናት ጸንቶ እንዲኖር፣ የኢትዮጵያዊነት መሠረት፣ቋሚ፣ ምሰሶ፣ ማገርና ጣራ በመሆን አገልግሏል፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያውያን መጨረሻ ግቡ ሥልጣንን መቆጣጠር የሆነ፣ መነሻ ምክንያቶቹ ወይም ሰበቦቹ ደግሞ አካባቢያዊነት፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ኢኮኖሚ፣ባህልና ርዕዮተ-ዓለም በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ልዩነቶችን በመምዘዝ በሚፈጠር ግብግብ አገሪቱ ባላቋረጠ የርስበርስ ጦርነቶች ውስጥ ያለፈችና ዛሬም ያለች መሆኑ፣ ታሪካችንና የምንገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ያስረዳል፡፡ ይህም በመሆኑ የአገራችን ታሪክ በአመዛኙ የጦርነት ታሪክ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የአገራችን ታሪክ የጦርነት መሆን፣ ሁሉንም ዜጎች በዕኩልነትና ማኅበራዊ ሰላም በሰፈነበት መልኩ እንዲኖሩ ለማድረግ አላስቻለም፡፡ሁለንተናዊ ዕድገትን ለማፋጠንና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት አላመቻም፡፡ ለተከታታይ ዕድገት ምቹ አልሆነም፡፡

ሁለቱ ጦርነቶች ማለትም የውጭ ወራሪዎችንና ቅኝ ገዥ ኃይሎችን የመከላከሉና የውስጥ የሥልጣን ግብግብ ጦርነቶች፣ በታሪካችን ውስጥ ሁለት ጉልህ ተቃራኒ ክስተቶች ጎን ለጎን እንዲጎለብቱ አድርጓል፡፡ የመጀመሪያው ክስተት የማፍረስ ሲሆን፣ ሁለተኛው የመገንባት ነው፡፡

የአገራችን የረጅም ዘመን ታሪክ፣ በተለይም ከአንደኛው እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ጨብጣው የነበረው የሥልጣኔ ደረጃና የቴክኖሎጂ ምጥቀት ዛሬ ከምንገኝበት የዕድገትና አጠቃላይ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸር ከላይ ከተገለጡት ሁለት ተቃራኒ ክስተቶች የማፍረስ ጎኑ እጅግ የበረታ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ የአገርን ዳር ደንበር፣ የሕዝብን ነፃነትና ሉዓላዊነት ለመከላከልና ለማስጠበቅ፣ እንዲሁም በሥልጣን ይገባናል ባዮች የተቀሰቀሱ የእርስበርስ ጦርነቶች ተገንብተው የነበሩ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የባህል፣ የማኅበራዊ፣የወታደራዊና የቴክኖሎጂ መፍለቂያ ተቋሞችን፣አሠራሮችንና ግንኙነቶችን ወዘተርፈ እንዳለ በማውደሙ የዕድገት ተከታታይነት እንዲቋረጥ በማድረግ፣ አገሪቱ የተገነባን በማፍረስና አዲስ መሠረት በመጣል ሽክርክሪት ውስጥ አስገብቶ ዕድገቷ የኋሊት እንዲጓዝ አድርጓል፡፡ ከዚህ ላይ ልንገነዘበው የመሚገባው ቁም ነገር፣ የውጭ ወራሪዎች አገራችን ለማጥቃት በተነሱ ቁጥር ለጥቃታቸው መግቢያ ቀዳዳ የሚያደርጉት በመካከላችን ያለውን ልዩነት በመጠቀም እንደሆነ ልብ ማለት ያለብን መሆኑን ነው፡፡ በአገራችን ረጅም ታሪክ ውስጥ በማዕከላዊ መንግሥት ላይ ያኮረፉ ተቃዋሚዎች ወይም የሥልጣን ተቀናቃኞች ለሥልጣን ሲሉ ብቻ፣ የውጪ ወራሪ ኃይሎች መሣሪያ በመሆን፣ መንገድ እየመሩ፣ ሥንቅ እያቀበሉ የአገሪቱን ነፃነትና ብሔራዊ ጥቅም ከፉኛ የጎዱ መኖራቸውን ታሪካችን ያስረዳል፡፡

ዕድገት የተከታታይ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ፖሊሲዎች ውጤት እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህ ተከታታይነት ደግሞ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ባህል ውስጥ እንኳን ትናንት ዛሬም በፖለቲከኞች ኅሊና ውስጥ ተገቢ ቦታውን ያገኘ ባለመሆኑ ዕድገት ለኢትዮጵያ በርቀት የሚታይ አድማስ ከመሆን አላለፈም፡፡

በአገራችን ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ጎልተው ከሚታዩት የጦርነት ክስተቶች ሌላኛው ጎን ጦርነቱ ልዩ ልዩ ጎሣዎችንና ነገዶችን እንዲዋሐዱና እንደ አንድ ሕዝብ የወል ታሪክ፣ የጋራ አገር፣ የወል ኢትዮጵዊ የማንነት ዕሴቶችና ተመሳሳይ ሥነልቦና እንዲመሠርቱና የልዩነት ግድግዳዎችን ደረማምሰው ኢትዮጵያዊ ዜጋ እንዲሆኑ ያስቻላቸው የግንባታ ሂደት ነው፡፡

በልዩ ልዩዎቹ ነገዶች መካከል የተፈጠረው አንድነት በአመዛኙ በሁሉም የጋራ ፍላጎት ሰጥቶ በመቀበልና ወስዶ በመመለስ፣ በተናጠልና በወል እንቅስቃሴ፣በተፈጥሮ ሳቢና ገፊ አስገዳጅ ኃይሎች ግፊት፣ በጋብቻ፣ በስደት፣ በፍልሰት፣ በጦርነት፣ በንግድ፣ በጉዲፍቻ፣ በሞገሳ፣ ወዘተርፈ አማካኝነት ተለንቅጦ የተዋሐደ

በመሆኑ፣ የተፈጠረው አንድነት በቀላሉ ለማፍረስ አልተቻለም፡፡ ኢትዮጵያ የብዙ ነገዶችና ጎሳዎች አገር ናት የሚያሰኛትም ይኸው እንዱን ነገድ ከሌላው ነጥሎ ለማቆም የሚያስችል መነጠያ የማንነት መከሰቻ ሁኔታ የሌለና ነገዶቿና ጎሳዎቿ  አንድነት የፈጠሩባት አገር በመሆኗ ነው፡፡

ይህ ግን በዛሬዋ ኢትዮጵያ፣ ያውም፣ አውሮፓ ወደ አንድነት እየተጠቃለለ ባለበት ታሪካዊ ወቅት፣ ለሰባ ዓመታት ተለያይተው የነበሩት ምሥራቅና ምዕራብ ጀርመን መልሰው በተዋሐዱበት፣ ሰሜንና ደቡብ የመኖች አንድ በሆኑበት፣ የምሥራቁና የምዕራቡ ዓለም የልዩነት አጥር የነበረው ርዕዮተ-ዓለማዊ ግንብ ተንዶ ዓለም በአንድ አመለካከት ሥር በተጠቃለለበት ዘመን፤ለረጅም ዘመናት እጅግ በተራዘመ ሂደት ልዩነታቸውን አጣበው በአንድነት የኖሩትን ነገዶችና ጎሳዎች የመነጣጠልና ታናናሽ መንግሥታትን የመፍጠር ጅምር ተጠናክሮ መቀጠሉን እያየን ነው፡፡ የቋንቋ መሥመር በማስመር አንዱ ከሌላው እንዳይገናኝ የማድረግና በጋራ ጥረት የገነቧቸውን የወል ዕሴቶች፣ ተቋሞችና አሠራሮች ሆን ተብሎ፣ ታስቦና ታቅዶ በማውደም ልዩነቶችን በማባዛትና በማራገብ፣ ኢትዮጵያ የምትባል አገርና ኢትዮጵያዊ የሚባል የዜግነት መታወቂያ ፈጽሞ እንዳይኖሩ እየተደረገ መሆኑን በገሐድ እያየን ነው፡፡

የአገራችን ጥንታዊ ሥልጣኔ፣ ጨብጣው የነበረው ዕድገትና በዓለም ላይ የነበራት ተሰሚነት፣ ያላት ጂኦ-ፖለቲካዊ አቀማመጥ፣ ያላት የውኃና ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ሀብት፣ በአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ላይ የተቀዳጀችው አንጸባራቂ ድል፣ ለጥቁር አፍሪካ ሕዝብ ነፃነትና በዓለም ለሚገኙ መላው የጥቁር ሕዝብ ነፃነት ያበረከተችው የአርአያነት ተግባር፣ በጥቅሉ ኢትዮጵያ ያላት ቁሳዊና ኅሊናዊ ሀብት አገራችንን የመከበሪያ፣ የመታፈሪያ፣የተሰሚነትና የተከታታይ ዕድገት መጨበጫ፣የሁለንተናዊ ብቃት ቋት ባደረጋት ነበር፡፡ የሆነው ግን የዚህ ተቃራኒው ነው፡፡ ተከታታይነትና ወጥነት ያለው ፖለቲካዊ ባህል፣ ተከታታይነት ያለው የኢኮኖሚ፣የፖለቲካና የማኅበራዊ ፖሊሲ አለመኖር፣ ጥንታዊ ሥልጣኔአችንን መሠረት ያደረገ ቴክኖሎጂ ለማዳበር አለመቻላችን፣ ያለንን የተፈጥሮ ሀብት አልምተን በጥቅም ላይ አለማዋላችን፣ ያለንን ካፒታል በአግባቡ መጠቀም አለመቻላችን፣ እነዚህ ሀብቶች ጠላት ገዝ በመሆን የጥቃት ዒላማ እንድንሆንና ለዙሪያ ገብ ችግሮችና ተዋራጅነት እንድንዳረግ አድርገውናል፡፡

**የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ጥሎብን ያለፈው የትውልድ ክፍተት፤**

የጣሊያን ፋሽስቶቸ ኢትዮጵያ በቆዩበት አምስት ዓመታት ውስጥ አገሪቱ የነበሯትን በመቶ ሚቆጠሩ የተማሩ ኢትዮጵያዊያንን አሳደው በመግደል እንደጨረሷቸው ይታወቃል፡፡ ይህ የጣሊያን ፋሽስቶች የተማሩ ኢትዮጵያውያንን መፍጀት፣ በተከታዩ ትውልድ ላይ በአጭር ጊዜ ሊሟላ የማይችል የትውልድ ክፍተት ፈጥሮ በመሔዱ፣ ተከታዩ ትውልድ ካለፈው የሚይዘው፣ ለመጪው በእርሾነት የሚጠቀምበት ሁለንተናዊ የአቅም ቋት ያሳጣ በመሆኑ፣ በአገሪቱ ዕድገት ጉዞ ላይ በምንም መልኩ ሊተመን የማይችል መጠነ-ሠፊ ጉዳት ማድረሱ ግልጽ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ፣ ከድል በኋላ አገሪቱ በዘመናዊ  የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ዜጎች ለማፍራት በርካታ ዓመታትን መጠበቅ ነበረባት፡፡ ከጣሊያን ከአገር መባረር በኋላ የመጀመሪያው ሐኪም ሆነው ከእንግሊዝ አገር የተመለሱትን ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስን አስተምራ ለሥራ ለማብቃት 15 ዓመታት  ወስዶባታል፡፡

በሌሎች የሙያ መስኮች የሠለጠኑትን ጥቂት ኢትዮጵያውያንን ለማፍራት በርካታ ዓመታትን እንድትጠብቅ ግድ እንዳላት የሥልጠናው ባሕሪይ ይናገራል፡፡ ይህ ከድል በኋላ ቀለም የቀሰመው የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ትውልድ አብዛኛው በነጉሡ-ነገሥቱ አስተደደር መዋቅር ውስጥ በመመደብ የሥርዓቱ ታማኝ አገልጋይ ሲሆን፣ ተከታዩ ትውልድ ከእርሱ በፊት ቀለም ቆጥረው የንጉሡ ታማኞች የሆኑትን በአድርባይነት፣ በአድኃሪነትና በጥቅመኛነት በመፈረጅ ራሱን ለሥር-ነቀል የማኅበራዊ አብዮት ለውጥ አዘጋጀ፡፡ ይህም ለዕድገት መሠላል የነበረውን ተከታታይነትና የዕሴት ቅብብሎሽ በመስበር አገሪቱና ትውልዱ ወደ ጥፋት አዘቅት ውስጥ ከተተ፡፡ አብዮቱ ሥረ-ነቀል በመሆኑ ትውልዱንና ነባር መልካም ዕሴቶችን ከሥሩ አፈለሳቸው፡፡ የተከታታይነት ሁለንተናዊ ፋይዳዎች ጠፉ፡፡ ዳግም የትውልድ ክፍተት ተፈጠረ፡፡ ትልዱ ላይገናኝ በርዕዮት ተፋታ፡፡ ሕዝቡ በቋንቋ ልዩነት ተከፋፈለ፡፡ የጥንቱ አንድነትና የኢትዮጵያዊነት ስሜት ትል የበላው አገዳ ሆነ፡፡ ምንም እንኳን የቅንጅት ለአድነትና ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ ብቅ ባለበት ወቅት፣ ላንድ ሰሞን፣ የማኅበራዊ አብዮት ነጣጥሏቸው የነበሩትን የአንደ ዘመን ትውልዶች በአንድነት ለአንዲት ኢትዮጵያ ኅልውና መጠበቅ ቆመው ቢታዩም፣ ይህ አንድነት ብዙጊዜ ሳይቆይ ወደነበረበት ፊትና ጀርባ ተመለሰ፡፡  ይህ የትውልድ የዕሴቶች ቅብብልና አብሮ የመሥራት ባህል አለመኖርና የተከታታይነት መቋረጥ ችግር ኢትዮጵያውያን ያልፈቱትና ሊፈቱትም ሙከራ ያላደረጉበት የችግሮች ሁሉ ቋት ነው፡፡ ይህም የአንዲት ጥንታዊትና ታሪካዊት አገር ጉዳይ፣ ተዝረክርኮ፣ እኛና እነሱ በመባባል ሁሉም በየፊናው እንዳሻው የሚጎትተውና የሚለጥጠው ክስተት በመሆን የአገሪቱን ችግር እየቆለለውና እያውሰበሰበው ይገኛል፡፡

**ዘመናዊ ትምህርት የፈጠረው ለአገሩ ባዕድ የሆነ ትውልድ፣**

ዘመናዊ ትምህርት ወደ አገራችን ከገባ አንድ መቶ ዓመት አስቆጥሯል፡፡ ትምህርቱ መቶ ዓመት ያስቆጥር እንጂ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባህል፣ ታሪክ፣ ትውፊት፣ዕምነት ወዘተርፈ.... ባዕድ በመሆኑ ቀለም የቀሰመው ትውልድ ከአገሩ ሁለንተናዊ ዕሴቶችና ፋይዳዎች እንዲፋታ አድርጓል፡፡ ዘመናዊ ትምህርት ከቀሰመው ትውልድ መካከል፣ በተለይም አመለካከቱ በግራ ዘመም ፖለቲካ የተቃኘው፣ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ነገር ሁሉ፣ ኋላቀር፣ አሉታዊ፣ የዕድገት ጠርና የዘመነዊነት የማይገፋ ጠላት አድርጎ በመመልከት ለሥር-ነቀል ለውጥ ሁለመናውን የሰጠ ሆነ፡፡ ይህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪካዊ ቁርኝት፣ የመንግሥት አመሠራረት ሂደት፣ በልዩ ልዩ ነገዶች መካከል ያሉ ነባርና ጊዜአዊ ችግሮች መነሻ ምክንያቶችን፣ በመካከላቸው ያሉ መስተጋብሮችንና ግንኙነቶች በሚገባ ያልተረዳው ትውልድ፣ ቅኝ ገዥዎች በአፍሪካ ሕዝብ ላይ እንዳደረጉት፣ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ሁሉ፣ መጥፎው ከመልካሙ

ሳይለይ መወገድ እንዳለበት አቀነቀነ፡፡ የጥፋት እጁንም አነሳ፡፡ ኢትዮጵያን የመሰለች ጥንታዊ አገር፣ ነባር ባህሏ፣ ዕምነቷ፣ ታሪኳ፣ ተቋሞቿ፣ ወዘተርፈ....አይረቡም፣ ጎታችና ኋላቀር ናቸው ብሎ መጥፋትና መወገድ እንዳለባቸው በማመን፣ የአንድነትና የኢትዮጵያዊነት መገለጫ የነበሩ የወል ዕሴቶችን ያላዳች ትክ እንዲወድሙ አደረገ፡፡

ከሁሉም በላይ ባለፉት 50 እና 60 ዓመታት ውስጥ ቀለም ቀመሱ ኢትዮጵያዊ ከነባራዊ የወል ኢትዮጵያዊ ዕሴቶች መውጣት ብቻ ሳይሆን፣ የአገሪቱ አንድነት መሠረት የሆኑትን ተቋሞች፣ ዕምነቶች፣ አሠራሮችና ግንኙነቶች በሥርነቀል ማኅበራዊ አብዮት አማካኝነት ከሥራቸው አፈለሳቸው፡፡ ከዚህ የተሳሳተ ግንዛቤ ተነስቶ ኢትዮጵያን ለመለወጥ የተነሳው ትውልድ፣የለኮሰው እሳት፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለአሥራ ሰባት ዓመታት ሲያባራ ወዳልቻለ የእርስ በርስ ጦርነት፣ መፈናቀል፣መገዳደልና መሰደድ የመከራ አዘቅት ውስጥ ከተተው፡፡ የዚሁ አፍራሽ ትውልድ አባልና የማፍረስ ሂደቱ ቀጣይ የሆነው፣ በቅኝ ገዥዎች ፖለቲካዊ አስተሳሰብና አመለካከት የተቃኘው ጽንፈኛው የወያኔ ጎሰኛ ቡድን በተራው ላለፉት 21 የአገዛዝ ዘመኑ አገሪቱ በታኳ አይታው ወደማታውቀው የጎሳና የሃይማኖት ግጭቶች መነኃሪያ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ የአገሪቱን ነባር ታሪክ በመሻር፣ "ኢትዮጵያ ከመቶ ዓመት ያልዘለለ ታሪክ ያላት፣ በዐፄ ምኒልክ ወራሪ ሠራዊት የተመሠረተች፤ ሕዝቡ በጋራ እንደአገር የሚያስተሳስረው ነገር የለም" የሚል የሸንበቆ አፈራ፣ የበሬ ወለደ፣ አስተሳሰብ ይዞ ሥልጣን በመሣሪያ ኃይል የያዘው ዘረኛ ቡድን፣የኢትዮጵያ መሠረት የሆነችውን ባሕረ ነጋሽን በኢትዮጵያ ቅኝ የተያዘች ናት በማለት እንድትገነጠል ከማድረጉም በላይ፣ ሕዝቡን በቋንቋ ከፋፍሎ በማደራጀትና አንዱ የሌላው ጠላት እንደሆነ በመስበክ ኢትዮጵያ የምትባል አገርና ኢትዮጵያዊ የሚባል ዜጋ እንዳይኖሩ እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ዘረኛ ቡድን፣ ዐማራ የተባለውን ነገድ፣ በአገሪቱ ከሚገኙት ነገድና ጎሳዎች መካከል ከፍተኛ ቁጥር ካላቸው ሁለት ነገዶች አንዱ የሆነውን ለይቶ፣ በአገሪቱ በተለያዩ ታሪካዊ ወቅቶች ተፈጠሩ ለተባሉ ችግሮች ሁሉ ተጠያቂ በማድረግ፣ ማንነቱን በጦረኛነት፣ በተስፋፊነት፣ በትምክህተኝነት፣ በወራሪነት፣ በኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት አቀንቃኝነት፣ በአንድነት ጠበቃነት፣ በጡት ቆራጭነት፣ በገዳ ሥራዓት አፍራሽነት በመፈረጅ የተቀነባበረ የዘር ማጽዳት ዘመቻ በመክፈት ኅልውናውን ለከፍተኛ አደጋ ጥሎታል፡፡

**በጎሰኞች የተዛባውና የተከለሰው የኢትዮጵያ ታሪክ፣**

ታሪክ የሚጻፈው የዛሬው ትውልድ ካለፉት ትውልዶች ስሕተቶች ተምሮ፣ ያለፉት ስሕተቶች በዛሬውና ወደፊት በሚመጡት ትውልዶች እንዳይደገሙ ለማድረግ፣ባለፉት ትውልዶች የተሠሩ በጎ ሥራዎችን በመንከባከብና ተከታታይነታቸውን በመጠበቅ የዛሬው ትውልድ የራሱን መልካም ሥራዎች አክሎባቸው አገሩን ወደ ተሻለ የዕድገት፣ የሥላጣኔና የልማት ደረጃ ለማድረስ የእውቀትና የጥበበ፣ የማንነትና የአጠቃላይ ማኅበረሰባዊ ግንኙነት ሰንሰለት በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የታሪክ ዕይታ ያለፈውን ታሪካችን መማሪያ ብቻ ሳይሆን፣ለዛሬው ማኅበረሰባዊ ሕይዎታችን መገንቢያ እንደ አንድ ሁነኛ ግብኣት በመሆን የዕድገትን ተከታታይነት እንድናስጠብቅ ይረዳናል፡፡ ዛሬ በዕድገትና በሥልጣኔ የገፉት አገሮች ለደረሱበት የዕድገት ደረጃና ለጨበጡት ሥልጣኔ ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ ያገለገላቸው፣ ያለፉ ታሪኮቻቸውን በቅጡ ከመረዳት አልፈው፣ ጎጂዎቹን በማስወገድ፣ ጠቃሚዎቹን በማዳበር ያከናወኑት ተከታታይነቱን የጠበቀ የትውልድ ቅብብሎሽ ተግባር የሰመረ መሆን ነው፡፡ በአንፃሩ ወያኔና በአምሳሉ የቀፈቀፋቸው የጎሣ ብሔርተኛ ድርጅቶች ታሪክን በመካድ፣ በመከለስና በማጣመም የልዩነት ማራገቢያ በማድረግ በሕዝብ መካከል የግጭቶች መቀስቀሻ፣የጠባብ ፖለቲካዊ ግባቸው መዳረሻ ሁነኛ መሣሪያቸው እያደረጉት ይገኛል፡፡ ባለፉት 21 ዓመታት የወያኔ ትግሬዎች አገዛዝ ውስጥ የዚህ የተጣመመና የተዛባ ሀሰት ድርሳን ውስጥ በማስገባት የግፍ ሰለባ የሆነው ዐማራ የተሰኘው ሠፊ ነገድ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህ ነገድ በነፍጠኝነት፣ በወራሪነት፣ በጨቋኝነት፣ በበዝባዥነት፣ በቅኝ ገዥነት፣ በኢትዮጵያ አንድነት ጠበቃነት፣ በኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት አቀንቃኝነት ጭምር በመወንጀል፣ ከፍተኛ የሆነ የተቀነባበረና ተከታታይነት ያለው የዘር ማጽዳት ዘመቻ ተከፍቶበታል፡፡ ዐማራው በግፍ ከመገደሉ፣ ከመታሰሩ፣ ከሥራ ከመባረሩ፣ ከመሰደዱ አልፎ በኢትዮጵያ ምድር መኖር አትችልም ተብሎ ከደቡብ፣ ከደቡብ ምዕራብና ከምሥራቅ የአገሪቱ ክፍል ቤት ንብረቱን ተነጥቆ እንዲባረር ተደርጓል፡፡ ይኸም ብቻ አይደለም፡፡ ሃይማኖታዊ ተቋሞቹ ሆን ተብሎ እንዲወድሙ እየተደረገ ነው፡፡ ታላቁ ገዳም የዋልድባ መታረስ፣ የዝቋላ አቦ መቃጠል፣ የተተለያዩ ቤተክርስቲያኖች መቃጠል፣ የከበሩ ንዋዬ ቅዱሳን መዘረፍ፣ በ1984 በምዕራብ ጎጃም መተከል አውራጃ በዲባ ጠና፣ ማንዱራ ጉንጉአ ወረዳዎች፣ ከ60 ሺህ በላይ የሆኑ የእስልምና እምነት ተከያይ ዐማሮች፣ ዐማራ በመሆናቸው ብቻ በቤንሻንጉል ክልል መስተዳድር አሰቃቂ ጥቃት ከማድረሱም በላይ 185 መስጊዶች እንዲወደወሙ ተደርጓል፡፡ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት የታገሉና ክቡር ሕይዎታቸውን ቤዛ ያደረጉ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ዐማራ በመሆናቸው ብቻ የወራሪነትና ነፍጠኝነት ስም ተለጥፎባቸው በስማቸው የተከፈቱ ተቋሞች ስማቸው እንዲለወጥ፣የቆመላቸው ሀውልት እንዲፈርስ ተደርጓል፡፡ በዐፄ ገላውዲዎስ ስም ይጠራ የነበረው የናዝሬቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በኃይለማርያም ማሞ ስም ይጠራ የነበረው ሆስፒታል፣ መጠሪያ ስሞች መለወጥ፣ ጂጂጋ ላይ ቆሞ የነበረው የደጃዝማች አፈወርቅ ወልደሰማዬት ሀውልት መፍረስ በአስረጅነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህን መሰል ተግባሮች ተጣምረው ሲታዩ ወያኔ ዐማራው በኢትዮጵያ ታሪክ የተጫወተውን ጉልህ ሚና በአሳፋሪነት መዝግቦ ያን ለማጥፋት ቆርጦ ተነሳ መሆኑን ብቻ ሳሆን፣ ዐማራ የተሰኘ ነገድ በኢትዮጵያ ምድር እንዳይኖር እያደረገ መሆኑን በዐማራው ላይ እየተፈጸሙ ያሉ የዘር ማጽዳት ዘመቻዎች ጉልህ ነቀቃሾች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ፣ ይህ በወያኔ ትግሬዎች ከ17 ዓመታት በላይ ባላሰለሰ መንገድ በዐማራው ላይ በግልጽ የተካሄደው ፀረ-ዐማራ ፕሮፓጋንዳ፣ ባለፉት 21 ዓመታት ደግሞ የመንግሥት ሥልጣን ጨብጦ ሁሉን በእጁ፣ ሁሉን በደጁ ካደረገ በኋላ እንኳን፣ የመንግሥትነት ባሕሪይ መላበስ ያቃተው ወያኔ፣ በዐማራው ላይ

የሰነቀውን ጥላቻና ለማጥፋት ያደረገውን ዝግጅት ሊያለዝብ አልፈቀደም:: በአካላዊ ጥቃት የታገዘውን ፀረ-ዐማራ ፕሮፓጋንዳ ቀጥሎበታል:: በመሆኑም የትውልድ አስተሳሰብና አመለካከት ቀራጭ በሆኑት ትምህርት መማሪያ ተቋሞች የሚማሩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናትና ወጣቶች የዐማራውን ነገድ በጭራቅ መስሎ የሚያቀርብ የታሪክ ትምህርት እንዲማሩ በመደረጉ፣ በመላው አገሪቱ የሚገኘው ዐማራ ያልሆነው ኢትዮጵያዊ ዐማራውን በጠላትነትና በጥርጣሬ እንዲያየው ከመደረጉም ባሻገር፣ የዐማራው ልጆች ራሳቸው በአባቶቻቸው ታሪክና ማንነት እንዲያፍሩ፣ እንዲሸማቀቁና አንገታቸውን እንዲደፉ እየተደረገ ነው:: ይህ ሁሉ የተቀነባበረ በአካላዊ ጥቃት የታገዘ የሥነ-ልና ጦርነት፣ በጊዜ ብዛት የዐማራውን ሕዝብ ከሰውነት ደረጃ ዝቅ በማድረግ ሊታዘንለት የማይገባው፤ ማንም ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ እንደ እባብ ራስ ራሱን ሊቀጠቅጠው የሚገባ፣ ሰብአዊነት የሌለው ፍጡር ተደርጎ እንዲቆር የማድረጉ ዘመቻ ተጠናክሮ የቀጠለ መሆኑ በግልጽ ይታያል:: ይህንን ዘርፈ ብዙ የሆነ በወያኔዎች የተቀነባበረ ፀረ- ዐማራ ቅስቀሳ ተከትሎ በበደኖ፣ በአርባ ጉጉ፣ በአሰቦት ገዳም፣ በወለጋ፣ በከፋ፣ በወልቃት፣ በጠገዴ፣ በጉራ ፈርዳ ወዘተርፈ በዐማራው ነገድ ላይ ሆን ተብሎና ታቅዶ የተፈጸመው ጥቃት፣ ወያኔ በዐማራ ላይ የከፈተው የዘር ማጽዳት ዘመቻ ውጤቶች ማመላከቻ ጭብጥ ማስረጃዎች ናቸው::

**የዐማራው ነገድ በተከታታይ ዘመናት የገጠመው መፈናቀልና የደረሰበት ጥቃት፤**

ባለፉት 500 ዓመታት ያለውን የኢትዮጵያ ታሪክ እንኳን ወስደን ብናይ፣ የዐማራው ነገድ በአራቱም የአገሪቱ ማዕዘኖች ተሰራጭቶ ከመኖሩ ጋር በተያያዘ፣ ኃይልን የተንተራሱ ሃይማኖት ቀመስ ወረራዎች፣ የኦቶማን ቱርኮችና የግብፆች የመስፋፋት ጦርነቶች፣ የአውሮፓ ቅኝ-ግዛት የወረራ ሙከራዎች፣ የኦሮሞ ፍልሰት፣ የታህሳሱ በነጀኔራል መንግሥቱ ንዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ያስከቱሉት የሰብአዊና የንብረት ውድመት በአባዛኛው ተጠቂ ያደረጉት የዐማራውን ነገድ እንደነበር የምናስታውሰው በመረረ ሀዘን ነው::

የ1966ቱን አብዮታዊ ለውጥ ተከትሎ በተካሄደው አጠቃላይ እንቅስቃሴ፣ በበዝባዥነት፣ በገዥ መደብነትና በጨቋኝ ብሔርነት ተፈርጆ የሰብአዊ እልቂት፣ የኢኮኖሚ ነጠቃ፣የፖለቲካዊና ማኅበራዊ መብቶች ገፈፋ መጠነ ሠፊ በሆነ መንገድ የተፈጸመበት የዐማራው ነገድ ነው:: ዘመኑና ትውልዱ የተከተለው የግራ ዘመም ርዕዮት ያስከተለው የኃይል አሰላለፍ፣ የፈጠረው "የቀይና የነጭ ሽብር" ፍጅት ዋነኛው ተጠቂ ዐማራው እንደነበር በግልጽ ይታወቃል:: የዚሁ ትውልድ ርዕዮት አቀንቃኝ የሆነው የወያኔ ቡድን ሥልጣን ሲይዝ፣ የጥቃት ዒላማው አድርጎ የተንቀሳቀሰው በዐማራው ነገድ ላይ መሆኑ ከፍሲል ተብራርቷል::

እነዚህንና መሰል ተግባሮችን አያይዘን ለማጤን ብንሞክር፣ የዐማራው ነገድ ከመቸውም ጊዜ በከፋ መልኩ ኅልውናው በከፍተኛ አደጋ ላይ የወደቀ መሆኑን እንገነዘባለን:: ዐማራው በሆደ ሠፊነት፣ በትዕግሥትና በአርቆ ተመልካችነት፣ ወያኔ በዐማራው ላይ የሰነቀውን የዘር ጥላቻ እያረገበ ወደ መቻቻልና ወደ አብሮነት ይመለሳል፣ ሥልጣናቸውን ሲያረጋግጡና ሲረጋጉ ወደ ዕውነተኛው ኅሊናቸው ይመጣሉ በማለት በከፍተኛ ተስፋ ቢጠብቅም፣ የጠበቀው ተስፋ ዕውን ሊሆን ካለመቻሉም በላይ፣ በዐማራው ላይ የከፋና የከረረ የዘር ማጽዳቱ ዘመቻ ተጠናክሮ በመቀጠሉ፣ ዐማራው ባለፉት 21 ዓመታት ያሳየው ትዕግሥትና ሆደ ሠፊነት ተፈላጊውን ውጤት ያላስገኘ በመሆኑ ትውልዱ ፈጽሞ ከመጥፋቱ በፊት ሌላ አማራጭ መከተል ግድ ብሎታል:: ይህም አማራጭ ዐማራው በዜግነት/ሲቪክ/ ድርጅት ተደራጅቶ ራሱን ከፈጽሞ ጥፋት መታደግ ነው:: ለዚህም ወያኔ በተከታታይና በሰከነ መልኩ ያደረሰበትን የዘር ማጽዳት ዘመቻ ተገቢ ምላሽ መስጠት የሚችል፣ የጥቃቱን ረቂቅነትና ሥልታዊነት የሚመጥን ግናዛቤና ዝግጅት ያለው የተጠናከረ ድርጅታዊ ኃይል ሲፈጥር ነው:: በመሆኑም የዐማራው ትውልድ ወያኔ እያደረሰበት ያለውን የተቀነባበረና የረቀቀ ሥልታዊ ዘር የማጽዳት ዘመቻ መመከት የሚችል፣ እየተሰነዘረበት ያለውን ጥቃት በበቂ ዝግጅትና ግንዛቤ ሊመራና ሊያስተባብ የሚችል ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የተሰኘ የዜግነት/ሲቪክ/ ድርጅት መመሥረት ግድ ብሎታል:: ሞረሽ ወገኔ የዐማራውን ነገድ በቋንቋና በዘር ማንነቱ ላይ ተመሥርቶ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚታገል ሳይሆን፣ ባለፉት ዘመናት ዐማራው ተከታታይነት ባለው ሁኔታ የተጣመመና የተዛባ፣ በውሸትና በጠላትነት በተራገበ የኢትዮጵያ ታሪክ ሰለባ የሆነበትን ጥላሸት በማገፈፍ፣ ዐማራው ዕውነተኛ ማንነቱን መልሶ የሚላበስበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው:: "ዐማራው በተከታታይ የአገዛዝ ሥርዓቶች ዋነኛ ተጠቃሚና ጨቋኝ ነው" የሚለውን የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን፣ ሆን ተብሎ የተራገበ ፀረ-ዐማራ ፕሮፓጋንዳ በማረም፣ ትውልዱ በሐቅ ላይ የተመሠረተ የታሪክ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግ የተዘጋጀ የሲቪክና የሙብት ተከራካሪ ድርጅት ነው::

ዐማራው ከኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ ባፈነገጠ መልኩ በዜግነት/ሲቪክ/ ድርጅት መልክ ለመደራጀት የፈለገው ወዶ፣ ፈቅዶና መርጦ ሳይሆን ተገዶ መሆኑን ጠላትም ሆነ ወዳጅ ይስቱታል አንልም:: ዐማራው ተገዶ በቋንቋና በዘር ማንነቱ ዙሪያ እንዲደራጅ ያስገደዱት መሠረታዊ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. ዐማራው በጠላትነት ተፈርጆ ላለፉት ሃያ አንድ አመታት ተከታታይነትና ያላባራ የዘር ማጽዳት ተግባር እየተፈጸመበት ያለ በመሆኑ፤
2. ለዘመናት ከኖረበት ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከደቡብ ምዕራብና ከመሀላ ኢትዮጵያ መባረሩ፤ በአገሩ ሙብት-የለሽ ዜጋ እንዲሆን በመደረጉ፣
3. ለዐማራው ነገድ ኅልውና፣ ሙብትና ነፃነት መገፈፍ ድምፁን የሚያሰማለት ተቆርቋሪ ድርጅት አለመኖሩ ናቸው::

እነዚህን ጥቃቶች ለመመከትና የዐማራውን ሁለንተናዊ መብቶችና ጥቅሞች ለማስከበር ከዐማራው ሌላ ማንም ሊኖር አይችልም:: ዐማራው የተቃጣበትን ኅልውናውን የማጥፋት ዘመቻ ስፋትና ትልቀት ተረድቶ፣ጥፋቱን ለመከላከልና ኅልናውን በአሰስተማማኝ

ሁኔታ ለመቀጠል መደራጀት ብቸኛ አማራጭ መሆኑን ተረድቶ፣ በሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ዙሪያ መሰባሰብ ይዋል ይደር የማይለው የመኖርና ያለመኖር ጥሪ ነው:: ይህን ሲያደርግም ተገዶ የተከተለው የአደረጃጀት መንገድ እንጂ፣ ምርጫው አለ መሆኑን ሳይዘነጋ ነው::

በመሆኑም ዐማራው በተከታታይ በፖሊሲ ተቀርጾ እየተፈጸመበት ያለውን ዘር ማጥፋት ተግባር ለመግታት ሲሞክር፣ የሚታገለው ፀረ-ዐማራ የሆኑ ፓርቲዎችን፣ ንቅናቄዎችን፣ ቡድኖችን፣ ግለሰቦችንና በፀረ-ዐማራነት የተቀረፁ ፖሊሲዎችን እንጂ፣ ማንንም ሕዝብ ወይም ነገድ አይደለም:: ዐማራው ኢትዮጵያ የሁሉም ነገዶች አገር ናት፣ በኢትዮጵያ ምድር አንድም ነገድ የግሉ የሆነ ግዛት የለውም ብሎ ስለሚያምን፣ ትግሉ በማንም ጎሳ ወይም ነገድ ላይ ያነጣጠረ አይደለም:: በኢትዮጵያ አንድነት ሁሉም ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፤ በመነጣጠላቸው ሁሉም ተጎጂዎች ይሆናሉ፤ ብለው የሚያምኑ የትግላችን አጋሮች ናቸው:: ትግላችን የሚያነጣጥረው የዐማራውን ነገድ ከሰብአዊ ፍጡር ደረጃ አውርደው ጭራቅ በማድረግ ኅልውናውን ለማጥፋት በተነሳው የወያኔ ትግሬዎች መንግሥትና የዚሁ ጎሰኛ ቡድን አመለካከትና ፍልስፍና የሚጋሩ ድርጅቶች ላይ ነው::

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት የዐማራውን ኅልውና ለማስጠበቅ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ሁሉ በመርሕ ደረጃ የሚከተላቸው ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማና ግቦች አሉት::

**1.ራዕይ፣**

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት፣ የዐማራውን ኅልውናና መብት ለማስጠበቅ የሚከተለውን ራዕይ ሰንቆ የሚንቀሳቀስ ነው::

1.1. ዐማራው በኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ እንደሌሎቹ ነገዶችና ጎሳዎች ሁሉ፣ ኅልውናው ተጠብቆ፣ እየደረሰበት ያለው መገደል፣ መሳደድ፣ መዋረድ፣ አንገት መድፋት፣ ከቀየው መፈናቀል ቆሞ፣ በፈለገው ቦታ፣ባሻው የሥራ መስክ የመኖርና ተንቀሳቅሶ መሥራት ሁለንተናዊ መብቱና ክብሩ ተከብሮና ተጠብቆ ማዬት፤

1.2. የሕዝባዊ የዜግነት መርሆዎች/ሲቪክ ናሽናሊዝም/ የተሰኙት የወል የዜግነት መገለጫ የሆኑ ዲሞክራሲያዊ ሥራዓትና የሕግ የበላይነት ሰፍኖ ማዬት፤

**2.ተልዕኮ፣**

2.1. ያንድ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መገለጫዎች የሆኑት የነባር ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መገለጫ የሆኑ የወል ዕሴቶችና ተቋሞች ተጠብቀውና ዳብረው፣ ሁሉም የኢትዮጵያ ነገድና ጎሳዎች፣ ሃይማኖቶችና አመለካከቶች በዕኩልነት የሚታዩበት፣ መቻቻል፣ መከባበርና መደጋገፍ የሰፈነባት ኢትዮጵያን ዕውን ማድረግ፤

2.2. በአክራሪ የጎሳ ፖለቲከኞችና ድርጅቶች አማካኝነት በዐማራው ነገድ ላይ የተካሄደውንና በመካሄድ ላይ ያለውን የዘር ማጽዳት ዘመቻ ማስቆም፤

2.3. ለዐማራው ነገድ ኅልውና ወሳኝ በሆኑ ዘርፎች ማለትም:- በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በባህል፣ በማኅበራዊ፣ በትምህርት፣ በጤና እና በመሳሰሉት መሥኮች ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚያደርጉ እንቅስቃሴዎችን ማቀነባበርና ዐማራው ተተቃሚ እንዲሆን ማስቻል፤

2.4. የኢትዮጵያ ኅልውና ምሰሶ ሆኖ የኖረው የዐማራው ነገድ ለወደፊቱ የአገሪቱ ኅልውና በአስተማማኝነት መቀጠል እንዲችል፣ ተቀራራቢና ተመሳሳይ ግቦችና ዓላማዎች ካሏቸው ድርጅቶች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች ጋር በመሆን ለጋራ ብሔራዊ ዕሴቶች ዳብሮ መቀጠል ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ፤

**3. የትግሉ ግቦችና ዓላማዎች፣**

3.1. ዐማራውን ፈጽሞ ለማጥፋት በወያኔና ተባባሪዎቹ የጎሳ ፖለቲካ ድርጅቶች የተያዘውን ዘመቻ ጨራሶ ማስቆምና ዐማራው በመላው ኢትዮጵያ መብትና ነፃነቱ ተጠብቆ የሚኖርበትን ምቹ ሁኔታዎች ማመቻቸት፤

3.2. የዐማራው ማንነት መገለጫ የሆኑ ዕሴቶችን ከጥፋት መከላከል፣ የጠፉትን በቦታቸው የሚመለሱበትን ሁኔታ መፍጠር፣

3.3. የኢትዮጵያን የግዛት ክልል፣ የሕዝቡን አንድነትና ሉዓላዊነት፣ የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ሚያስከብር፣ ሰላም፣ ነፃነት፣ ዕኩልነትና ፍትሕን የሚያረጋግጥ የምዕላተ ሕዝቡን ሁለንተናዊ ፈቃድ ያገኘ ዲሞክራሲያዊ ሥራዓት ለመመሥረት ከሚታገሉ ኃይሎች ጎን በመሰለፍ የበኩላችን ያልተቆጠበ ድርሻ ማበርከት፤

3.4. የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በአገሪቱ ብሔራዊ ትቅም፣ የግዛት አንድነት፣ በሕዝቡ መብትና ነፃነት ላይ ያደረሰውንና በማድረስ ላይ ያለውን ጥፋትና የፈጸመውን አገራዊ ክህደት ለዓለም ማኅበረሰብ በማጋለጥ አገዛዙ በሕዝብ አመጽ የሚወገድበትን አቅም መፍጠር፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የኔ የሚለው ዲሞክራሲያዊና ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲመሠረት መታገል::

4. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ወደነዚህ ግቦች ለመቃረብ አስፈላጊ የሆኑ የትግል ሥልቶችን ይጠቀማል:: በዚህም መሰረት ሞረሽ የሚከተሉትን ሥልቶች በተለዋዋጭነት ይከተላል::

4.1. ዐማራው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ያለውን ቦታ፣ የተጫወተውን ሚና በተመለከተ የተነዛውን የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን፣ ሆን ተብሎ የተራገበ የጠላት ፕሮፓጋንዳ

በዕውቀት፣ በተጨባጭ ሐቅና በጥልቅ ጥናት ዕውነታውን ማሳወቅ፣ ስለኢትዮጵያ ተጣሞ የቀረበውን ውሸት በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ ማጋለጥና ማምከን፤

4.2. የዐማራውን ነገድ ከማንም በላይ የጥቃት ሰለባ ያደረገው፣ የወያኔ ትግሬዎች አገዛዝ ፖሊሲ ቀደም ሲል በታላቁ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ መሪነት የኢትዮጵያ ሕዝብ በዐድዋ ላይ የተጎናጸፈውን ድል ተከትሎ በወጣው የጣሊያን ቅኝ ገዥዎች የጠላትነት አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህም የጣሊያን ቅኝ ገዥዎች አስተሳሰብ የሰረጸው ወያኔ ቡድን፣ “በዐድዋ ድል የነሳን የዐማራ ነገድ ተወላጅ የሆነው ዐፄ ምኒልክ ያስተባበረው ጦር ነው፡፡ ዐማራ የተባለው ሕዝብ የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ ዋና መሠረት ነው፡፡ ስለሆነም ዐማራውን ብናጠፋው ኢትዮጵያዊነት የሚለውን ማንነት እናጠፋዋለን፡፡” የሚለውን ዐማራውን ብቻ ሳይሆን መላዋ ኢትዮጵያን አጥፊ የሆነውን የጠላት ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ተንቀሳቀሰ፡፡ ይህ አስተሳሰብ ኢትዮጵያ ብትጠፋ ከዐማራው ውጪ ያሉትን በርካታ ነገድና ጎሳዎች አያስጨንቅም ወይም ግድ የላቸውም የሚል ቋሚ መልዕክት የሚያስተላልፍ በመሆኑ፣ የሌሎቹን ነገድና ጎሳዎች የአገር ፍቅርና ለኢትዮጵያ አንድነትና ነፃነት አነሰም በዛም የከፈሉትን መስዋዕትነት ዋጋ የሚያሳጣ የከፋፍለህ ግዛው የቅኝ ገዥዎች አስተሳሰብ እንደሆነ ይስቱታል አንልም፡፡ በጥቅሉ ወያኔና አጋር ድርጅቶቹ ባለፉት ዘመናት ዐማራን፣ አማርኛ ቋንቋን፣ የዐማራን ባህልና ታሪክ ለማጥፋት ያደረጉት ጥረት ከዚህ የጣሊያን የቅኝ ግዛት አስተሳሰብ የተቀዳ፣ አስተሳሰቡ ዐማራውን ብቻ ሳይሆን፣ በመላው ኢትዮጵያ የግዛት ክልል ውስጥ የሚገኙ ነገድና ጎሳዎች ሁሉ ጠራርጎ የሚያጠፋ እንደሆነ የወያኔ አጋር የሆኑ የየጎሳው ድርጅቶች ልብ ያሉት አይመስልም፡፡ ይህን የተሳሳተ አመለካከት ማምከን፡፡

4.3. ከጣሊያን ወራሪዎች ተቀድቶ በኤርትራ የቅኝ ግዛት ተወላጆቻቸው አማካኝነት ወደ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንቅስቃሴ ሰርጎ የገባው አፍራሽና ፀረ-ኢትዮጵያ አመለካከት፣ በሚሲዮን ትምህርት ቤቶችና በተለይም ኢትዮጵያን ለማፍረስ ቀን ከሌሊት ይደክሙ ከነበሩ የምዕራቡ ዓለም የሥነ-ሰብዕ ምሁራን (አንትሮፖሎጂስቶች)፣ እንዲሁም በሴማዊ ጥናት ላይ የተሰማሩ የምዕራቡ ምሁራን አማካኝነት ስለኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣ ባህል፣ ጎሳና ነገዶች፣ እንደዚሁም ዐማራው በኢትዮጵያ ታሪክ ስለተጫወተው ሚና ይቀርቡ የነበሩት የተጋነኑ፣ የተዛቡና አፍራሽ አስተሳሰቦች፣ዛሬ ዐማራውን የጥቃት ዒላማ ላደረገው የወያኔ ትግሬዎች የአገዛዝ ፖሊሲ ጥብቅ መሠረቱ እንደሆነ ይታመናል፡፡ እነዚህንና መሰል ከአንድ መቶ ዓመታት በላይ በኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ በዘመናዊነት ስም ተሰንቅረው የኢትዮጵያዊነት ማፍረሻ መሣሪያ የሆኑ፣ሥር የሰደዱ የቅኝ ገዥዎች ቅኝት ያላቸውን አመለካከቶችና አስተሳሰቦች በመረጃና በዕውቀት ላይ በተመሠረተ ጥናት ዋጋ ቢስ ማድረግ አንዱና ዋናው የቅርብን ሆነ ረጅም ጊዜ ትልም ነው፡፡

4.3.1. ዛሬ በማናቸውም ደረጃ እንዲከስም እየተደረገ ያለውን የዐማራው ነገድ ዋና መገለጫ የሆኑትን ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ ትውፊቱን መንከባከብና ለተተኪው ትውልድ የማንነቱ መገለጫ የሆኑትን ቋንቋውንና ባህሉን፣ ታሪኩንና ወጉን እንዲያውቅ ማድረግ፣ የዐማራው ባህልና የዕውቀት ምንጭ የሆነውን ግዕዝ ትውልዱ የሚማርበትን ሁኔታ መፍጠር፣ ስደት የሚገኙ የዐማራው ልጆች ታሪካቸውን፣ ባህላቸውንና ቋንቋቸውን የሚማሩበትን መንገድ ማመቻቸት የሞረሽ ወገኔ ዐይነተኛ ተግባሩ ነው፡፡

4.3.2. የታሪክ፣ የንባብና የባህል ክበቦችን በአገር ቤትም ሆነ በውጪ አገር በማቋቋም ትውልዱ ዕውነተኛ ታሪኩንና ባህሉን እንዲያውቅ ማድረግ፣ በተለያዩ ሥርዓቶች የተጣመመውን ያገሪቱን ታሪክ ማቃናት፣

4.3.3. ዐማራው እየተፈጸመበት ያለው የዘር ማጽዳት ዘመቻ ወዴት እያመራ እንደሆነ በቂ ግንዛቤ ትውልዱን ማስጨበጥ፤ እንደለፈው ጊዜ የዐማራው ወጣት በሰርጎ ገቦች፣ በመሰሪ ጎሰኞች፣ በኅብረብሔራዊ ድርጅትነት ስም በዐማራው ኅልውናና ማንነት ላይ በመደራደር የየግላቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ለማረጋገጥ በሚጥሩ ኃይሎችና ቡድኖች በመታለል እንዳለፉት ሁሉ መረማመጃ እንዳይሆን፣ እንዳይበለጥ፣ እንዳይዘናጋ ያላሳለሰ ጥረት በማድረግ በሣይንሳዊ ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ይጥራል፡፡

4.4. የወያኔ ትግሬዎችን አገዛዝ ለመጣል የሚደረገውን ትግል ማገዝ፣

4.4.1. የተለያዩና ከዐማራው ባህልና ዕምነት ጋር የተቆራኙ አሠራሮችን በማጥናት ሕዝባዊ ዕምቢተኝነትን መፍጠር፣ የወያኔና የሥራዓቱ ደጋፊዎች ላይ ማኅበረሰባዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሃማኖታዊ ማዕቀቦችና ማግለሎችን በመጣል ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሥነ-ልቦና ጥቃት መፈጸም፡፡ ለዚህም እምብዳዴ የተባለውን በዐማራው ባህል ውስጥ በስፋት የሚታወቀውን የማግለያ ዘዴ በሥራ ላይ የሚውልበትን መንገድ በማጥናት ዐማራው ተግባራዊ እንዲያደርገው ተግቶ መሥራት፡፡

4.5. በዐማራው ነገድ ላይ የተፈጸመበትንና እየተፈጸመበት ያለውን ጥቃት ማጋለጥ፤

4.5.1. እስካሁን ድረስ በዐማራው ላይ የተፈጸሙ የዘር ማጥፋት ድርጊቶችን በመመዝገብ አግባብ ላላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በማቅረብ አስፈላጊው ፍትሕ እንዲገኝ መጣር፤

4.5.2. የወያኔን አገዛዝ የሚያግልጥ የተጠናከረ ዲፕሎማዊ ሥራ መሥራት፤

4.6. በዐማራው ላይ እየደረሰ ያለውን የወያኔንና መሰል ድርጅቶች ፀረ-ዐማራ ተግባር ማምከን፤

4.6.1. በዐማራው ላይ እየተፈጸመ ያለውን የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ ዐማራው ተደራጅቶ በተቀነባበረ መንገድ ራሱን ከጥቃት ሊከላከል የሚችልበትን የሁለንተናዊ አቅም ባለቤት እንዲሆን የተጠናከረ የማደራጀት ሥራ መሥራት፤

4.7. ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ከሌሎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት፣

4.7.1. የዐማራው ነገድ እየተካሄደ ባለው ዲሞክራሲያዊ ትግል አካል ሆኖ፣ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነት፤ኢትዮጵያ አንድነትና ለሕዝቡ ሉዓላዊነት መረጋገጥ ከሚታገሉ ኃይሎች፣ የዐማራውን ነገድ በጠላትነት ከማይመለከቱ ወይም የፖለቲካ ሥልጣን መረማመጃ አድርገው ከማያዩት ማናቸውም ድርጅቶች ጋር ሁሉንም ኢትዮጵያውያንን የጋራ ጥቅም በሚያስከብሩ ጉዳዮች ዙሪያ የሚጠበቅበትን ሁሉ በብቃት ለመወጣት የበኩሉን ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል፡፡

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት እነዚህን ራዕዮቹን፣ተልዕኮዎቹን፣ ዓላማና ግቦቹን ለማሳካት በሚጥርበት ወቅት፣ ለመሆኑ ዐማራ ማነው? ብለው ለሚጠይቁ ወገኖች፣ በሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ዛሬ በሚገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ዐማራ ማለት የሚከተሉትን የሚያሟላና የሆነ ነው፡፡ እነዚህም፡-

1. በዐማራነቱ የሚያምን/የምታምን፣
2. ዐማራው ከሌሎች ተነጥሎ እየተጠቃ ያለ መሆኑን የተረዳ/ች፣ ይህንም ጥቃት ተደራጅቶ መከላከል ተገቢ ነው ብሎ/ላ ለትግሉ ዝግጁ ሆነ/ች፤
3. በተለያዩ ጊዚያት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ሊያጠፉ የተነሱ ኃይሎች የጥቃት ዒላማ ሆኖ ከፍተኛ ጥቃት የደረሰበት ዐማራው መሆኑን የተገነዘበ/ች፣
4. ባለፉት 21 ዓመታት የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በአውራ ጠላትነት ፈርጆ "ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ፣ አድኃሪ፣ በዝባዥ"፣ የሚሉ ስሞች ተሰጥተውት፣ ዐማራው በግፍ መገደሉን፣ መታሰሩን፣ ከሥራ መባረሩን፣ የመማር ዕድል እንዲነፈግ መደረጉን፣ ለዘመናት ከኖረበት ቀየው በግፍ መባረሩን የተረዱ፣ ያወቁና ይህ ድርጊት መቀጠል የለበትም ብሎ የሚያምን/የምትምን፣
5. የኢትዮጵያ አንድነት በነገዶቿና በጎሳዎቿ ዕኩልነትና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበርና ዳብሮ መቀጠል አለበት ብሎ የሚያምን/የምታምን፣
6. ኢትዮጵያ የሀወርታዊ ሕዝብና አገር ሆና የኖረች፣ በአገሪቱ ግዛት ውስጥ አንድም መሬት በብቸኝነት ለአንድ ነገድ ወይም ጎሳ የተሰጠ ወይም የተያዘ የለም፤ ኢትዮጵያ የሁሉም ነገዶችና ጎሳዎች የጋራ አገር ናት፣ ማነኛውም ግለሰብ በፈለገው አካባቢ የመኖርና የመሥራት መብቱ የተረጋገጠ መሆን አለበት ብሎ የሚያምን/የምታምን፤
7. የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ምሥረታ ሂደት በዓለም ከታየው የተማከለ መንግሥት ምሥረታ የሚለየው በቦታ፣ በጊዜና በአድራጊ ግለሰቦችና ኃይሎች እንጂ፣ ሌላው ሁሉ ሂደት በጊዜው ከነበረው የዕድገትና የአመለካከት ደረጃ አንፃር ሊታይ ይገባል ብሎ የሚያምን/የምታምን፤
8. ዐማራው በወደፊቷ ኢትዮጵያ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ቁጥሩና በታሪክ የተጫወተው ሚና ሊያስገኝለት የሚችለውን ተገቢ ድርሻ ሊያገኝ ይገባዋል፣ ለዚህም እታገላለሁ የሚል/የምትል፤
9. የግለሰብ ነፃነት የዲሞክራሲና የሕግ ሥርዓት ማገርና ዋልታ ነው ብለው የሚያምን/የምታምን፣
10. የሞረሽን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለ/ች ናቸው፡፡

***ዐማራን ከፈጽሞ ጥፋት እንታደግ!***

***ዐማራነት ኢትዮጵያዊነት ነው!***

***ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!***